## ዜና መፅሔት

የወያኔ አገዛዝ የገባበትን ቀውስ ለመሸፈን ልዩ ለዩ ርዕሶችና ጉዳዮችን እያደመቀ በማቅረብ ቢፍጨረጨረርም መሰረታዊ ችግሮቹ አፍጠው መምጣቸውና በሕዝብ ዕይታ መግባታቸው አልቀረም። በዚህ በሚያልቀው ሳምንት ውስጥ የወያኔ ጦር የሐረር ከተማን በቢአርና በታጠቁ ወታደሮች ወጥሮ ከምሽት ጀምሮ እስከ እኩለ ሌሊት ፍተሻ ሲያካሂድ መቆየቱ ታይቷል። ምክንያት? የወያኔ የመሳሪያ መጋዘን ባልታወቁ ሰዎች በመዘረፉ። የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ ከባድ መትረየሶችና አዳፍኔዎችም ጠፉ የተባለ ሲሆን እስካሁን ዘረፍኩ ያለ የታጠቀ ፀረ ወያኔ ድርጅት ባለመደመጡ ምናልባትም ዝርፊያ የተባለው የወያኔ የራሱ ሴራ ይሆናል የሚለው ን ጥርጣሬ አጠናክሮታል። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የነፍሰ ወከፍ ክላሽንኮቭ ጠመንጃ ዋጋ 10 ሺ ብር ወይም ከዚያም በላይ ገብቷልና ወያኔ ራሱ በቀጥታና በተዘዋዋሪ በመሳሪያ ሽያጭ ላይ መሰማራቱ ምስጢር አይደለም። የወያኔ ነጋዴዎች የጦር መሳሪያ ሸጠው በወዲያው ደግሞ ጠቁመው ገዢውን እያስያዙ መሆናቸው ታይቷል። ሐረር ተዘረፈ የተባለው መጋዘን ብዙ ከባድ መሰሪያዎችም ነበሩበት የተባለ ሲሆን የወያኔ ጦር በጄኔራል ገብሬ መሪነት በሶማሊያ በመሳሪያ ሽያጭ በሙስና ተሰማርቶ ነበር የሚለውን ዘገባ ስናስታውስ የወያኔ አገዛዝ ገንዘብ እስካገኘ ጠላት ለሚላቸውም ሁሉን ከመሸጥ ወደ ኋላ እንደማይል ግልፅ ይሆንልናል። የወያኔ አገዛዝ በርካታ መሳሪያዎችን ወደ ትግራይ አጓጉዞ መጋዘን መክተቱም የሚታወቅ ነው።

የመለስ ዜናዊ ቡድን ስርዓቱ የገባበትን ቀውስ ለመሸፈን በተለይም ረሀቡን፣ የውጭ ንግድ ክስረቱን፣ የኑሮ ውድነቱን ወዘተ ለመደበቅ በሚል ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የሚያስተጋባው ጉዳይ በመጪው ግንቦት 2002 አካሂዳለሁ ያለውን ምርጫ ይመለከታል። አራት ድርጅቶች ማለትን የልደቱ ኢዴፓ፣ በኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው መኢአድ፣ የአየለ ጫሚሶ ቅንጅትና የመለስ ዜናዊ ኢሕአዴግ ተብዬ ወያኔ በጋራ የምርጫ ስነ ስርዓት ደምብ ላይ ተስማማን ብለው መፈራረማቸው በወያኔ መገናኛ ብዙሀን ሲናፈስ ቆይቷል። በመሆኑም ወያኔ እንዳቀደው የሕዝቡ ጎራ በተወሰነ ደረጃ በውዠንብር መተራመሱ ሊታይ ችሏል። መኢአድ ለምን ይህን መለስተኛ ሰነድ እንደፈረመ ለማስረዳት ቢሞክርም ብዙዎች ደግሞ የዚህ ድርጅት መሪዎች የሕዝብን ዓላማ ትተውና የ1997ኡን ሰማዕት ረስተው ጎጂ አቀዋም ወሰዱ ይላሉ። ይህ ንትርክ ወያኔ እንዳቀደው ሁሉ ከወያኔ ወፍጮ ባቄላ የሚያቀርብ ሆኗል። የተደረገወ ስምምነት በስነ ስርዓት ነጥቦች ላይ ሲሆን ብዙዎቹ እነዚህም ነጥቦች ለወያኔ የሚጎረብጡ አይደሉም ተብሏል። የምርጫ ው ህግ ይለወጥ የምርጫው ቦርዱ ነፃ ይሁን ጥያቄ አልተነሳም። መሰረታዊ ቅድ ሁኔታዎች ወደ ጎን መተዋቸው ደግሞ ግልፅ ነው። ሌላም ሌላም። ይመጣሉ የተባሉትም የምርጫ ታዛቢዎች ለመለስ ተስማሚ የሚሆኑት ናቸው። የወያኔ አገዛዝ አሁንም ቢሆን ተቃዋሚ ሀይሎችን ደገፉች ሁ ብሎ አፈና እያካሄደ ስለሆነ ከተፈራራሚዎች አንዱ መኢአድ ታሰሩብኝ ያላቸውን እስረኞች ስለማስፈታት ጥረት መጀመሩን አስታውቋል። ለመሆኑ ወይዘሪት ብርቱካን ትፈታ የሚል

ቅድ.መ ሁኔታ ቀርቧል? ቀደም የተያዙት እነ አበራሽና ፀጋዬ ደብተራውስ? ምንምፍንጭ የለም፡
፡ ስማቸውም አልተነሳም።የቀድሞው መንግስት ደጋፊ ተብለው አለፍርድ እሳከሁን የሚማቅቁት
ስ? ከ1997 ጀምሮስ በዴዴሳ፤ ዝዋይ ወዘተ የታገቱትስ? የወያኔ አገዛዝ ግን ከምርጫው በፊት
ወይዘሪት ብርቱካንን እፈታታለሁ ብሎ በአደናጋሪ ዜና አሰራጭ ተቋሙ ማለትም ባዶ ሶስት
አማካኝነት እያሰራጨ ነው።የወይዘሪት ብርቱካን መፈታት ከቤተሰቧም አንፃር ቢሆን መልካም
ዜና ሊሆን ቢችልም ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ባልተፈቱበት ሁኔታ የወያኔ ፀረ ሕዝብነት
ሊለዝብ የሚችልበት መንገድ አለመኖሩ ግልፅ ነው። ድርጅቶችም የራሳችን እስረኛ እንጂ
ሌላው ጉዳያችን አይደለም ማለታቸው አስተዛዛቢ መሆኑ አልቀረም።

ምርጫ የሚሉት በአንድ በኩል ሲሆን ትጥቅ ትግል የሚሉት ክፍሎች ደግሞ የት ደረሱ ለሚለው
ብዙ አመርቂ መረጃ የለም። በሻዕቢያ የሚደገፉት ሀይሎች ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ አይደ
ለም። ሻዕቢያ በበኩሉ በቅርቡ ባወጣው መግለጫ ለኢትዮጵያ አንድነትና ጥንካሬ ደጋፊ መሆኑን
ገልጿል።ታዛቢዎች ግን መገንጠል ለሚሉተ ኦነግና የኦጋዴን ግንባር የሚሰጠውን ድጋፍ ከማንሳ
ታቸው ሌላ ለምን ሻዕቢያ ከህቀኛና ሕዝባዊ ብሔራዊ ድርጅቶች ጋር አልተያያዘም የሚለው
ጥያቄ ማንሳታቸው አልቀረም። ቢሆንም የትጥቅ ትግሉ ተጨባጭ የዛሬ ሁኔታ የጠነከረ ሆነ
አልሆነ ይህን የትግል ስልት ለማዳበር ብዙ መደረግ አንዳለበት ይታያል።

ለወያኔ ሥልጣን ላይ መውጣት ከፍተኛውን ድርሻ የተወጡት ባእዳን ኃይሎች እንደነበሩ ሰፊው
የኢትዮጵያ ህዝብ በክፉ ትዝታው በቁጭት የሚያስታውሰው ነው። ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣም በኋላ
እንዲደላድልና ሥልጣኑን እንዲያጠናክር የረዱት ባእዳን ሃይሎች መሆናቸው ይታወቃል። ሰሞኑን
አይን ባወጣ መንገድ ተቃዋሚ ሃይሎች ላይ ግፊት ጫና በማድረግ የቧልቱን ምርጫ እንዲያካሄዱ
ማድረጋቸው ምን ያህል ወያኔ የእነሱ ጥቅም አስጠባቂ መሆኑና ይህንን ኃይል በስልጣን ለማቆየት
የሚችሉትን ሁሉ ከማድረግ እንደማይመለሱ ያሳያል ሲሉ ታዛቢዎችን ያስገነዝባሉ።

ባለፈው ሰሞን የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስዩም መስፍን ከአሜሪካን አቻው ከሂላሪ ክሊንተ
ን ጋት በአሜሪካ ተገናኝቶ መወያየቱን በተመለከተ የወያኔ አገዛዝ ብዙ ለፍፏል። የኦባማ አስተዳ
ደፈር ይወደናል ይደግፈናል በሚል ለመመፃደቅና በተለይም የአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያ
ነፃነት የሚሉትን የስፈኞች ተስፋ ለማስቀረጥ። ሀቁ ሲነገረ ግን ስዩም መስፍን በጠየቀው መሰረት
የአሜሪካው ባለስልጣን ብታናግረውም ብዙ ቁም ነገር አለመወያያታቸው ታውቋል። ሆኖም
የአሜሪካ መንግሥት ጥቅሙን ያስቀድማልና መጋዣ የሆነውን የመለስ አገዛዝ እየደገፈ መቀጠሉ
የሚታወቅ ነው።

ከሰሞኑ ከወያኔ አባላት አካባቢ እያፈተለኩ ከሚደመጡ መረጃዎች በወያኔ ውስጥ መሸበርና
መርበትበት መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል። በአህያ ቆዳ የተሰራ ቤት ጅብ በጮኸ ቁጥር
እንደሚባለው በአሁኑ ወቅት በወያኔ ውስጥ ነባር አባላትም ሆኑ አዲስ አባላት ድርጅታዊ ሥነ
ምግባርን ሲጥሱ እየተስተዋለ ነው። የወያኔ አባላት ፣ ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ እርከን ያሉ የስለላው
ክፍል አባሎች፣ ቱባ የመንግስት አባሎች ሚንስትሮችም ጨምሮ ከውስጥ ቅሬታቸውና ብሶታቸው
በመነሳት ይመስላል ድርጅታችን እያሉ የሚጠሩትን ድርጅት ሚስጥር ቦታና ጊዜ ሳይመርጡ

እንደሚያወሩ  ታዛቢዎች እየመሰከሩ ያለበት ሁኔታ ነው። በድርጅታዊ ስብሰባዎቻቸው ላይ አለመተማመንና እርስ በእርስ የመዘራጠጥና የመናናቅ ስሜቶች በየመድረኮቻቸው ለይ መታየት ከጀመረ ውሎ ማደሩን አንዳንድ ውስጥ አዋቂ ምንጮች  ያጋልጣሉ። ከሱዳን ጋር በሚስጥር የድንበር ድርድር በከፍተኛ የወያኔ ቁንጮዎች መደረጉን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ  ከተቃዋሚዎች የመገናኛ ምንጮች መስማታቸው ብዙዎቹን የወያኔ ባለስልጣናት ያስቆጣና አለመተማመኑን እያሰፋ መምጣቱን ውስጥ አወቆች ይናገራሉ። በተያያዘ ዜናም በወያኔ ደህንነት በኩል ከፍተኛ ችግር እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። ለወያኔ ደህንነት አባላት ለሥራ ሲሰማሩ የሚከፈላቸው ክፍያ አንድ ወጥ አለመሆኑ ጉምግምታ ከፈጠረ ውሎ አድሯል። ለትግራይ  ተወላጆች የደህንነት አባላት የሚከፈለው ክፍያ ከሌሎቹ በሦስት እጅ ስለሚበልጥ ሌሎች ደህንነቶች ቅር እንደተሰኙና ሥራቸውንም በአግባቡ መወጣት እንዳልቻሉ ቅርበት ካላቸው ምንጮች መረዳት ተችሏል።  ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደህንነት ጉዳይ ሀላፊዎችን እያሳሰበ የመጣ ሌላም ችግር መኖሩ ታውቋል። ከታች ወደ ላይ የሚተላለፋ የስለላ መረጃዎች አለመኖርና  ያሉትም ቢሆኑ እጅግ የተዛቡ በመሆናቸው በተለያዩ  እርከን ላይ የተቀመጡ ሀላፊዎችን እያስጨነቀ እያሳሰበ መምጣቱ ለማውቅ ተችሏል ። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሲባል ወያኔ ተንቀሳቃሽ መረጃ ሰብሳቢ ቡድን በማደራጀት በተለያዩ አካባቢዎች ማሰማራቱን  አሰማርቷል። ይህ ዐይነት አሠራር በስፋት የተጀመረው ወያኔ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደረገብኝ ካለበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ። በወቅቱ ያልተያዙ የጦር መኮንኖችን ለመያዝ ወደ ምስራቅ፣ ደቡብ፣ ምዕራብና ሰሜን የሀገሪቱ ክፍሎች በርካታ የደህንነት ቡድኖች ተሰማርተው እንደነበርና ከዚያም በኃላ ይኸው አሰራር እስከዛሬም እንደቀጠለ ይነገራል። በዚያን ጊዜ በሁሉም አቅጣጫ የተሰማራው የደህንነት ቡድን ካለውጡት መመለሱና በተለይ እነ ኮሎኔል አለበል ከሀገር ሲወጡ ከሚከታተሏቸው የደህንነት አባላት ጋር በቅርብ እርቀት አብረው እየተጓዙ እንደነበር እንደተሰማ አለመተምመኑን እያሰፋው እንደሄደ ለማወቅ ተችሏል።

የወያኔ የጤና አጠባበቅ ከአፍሪካ ከመጨረሻዎቹ ተርታ እንደሆነ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገለጹ። ፖሊዮን ለፖለቲካ መጠቀሚያ በማድረግ እንደጠፋ እየተገለጸ ባለበት በምስራቅ ኢትዮጵያ በበሽታው የተጠቁ ህጻናት መታየታቸው ወያኔ ከህዝብ ጤና መጠበቅ ይልቅ የሚያስጨንቀው የራሱ የፖለቲካ ሥልጣን መጠበቅ ለመሆኑ ዐይነተኛ ማስረጃ ነው። ሰሞኑን የወያኔ የፕሮፓጋንዳ አውታሮች ወያኔ ከሱ በፊት ከነበሩት ሁለት መንግስታት ለጤና አጠባበቅ እየሠራ መሆኑን የሚያቀርቡት ቅስቀሳ ህዝብን ከመናቅ እንደሚቆጠር ብዙዎች በምሬት ይናገራሉ። አንኳር አንኳሩን ለማንሳት በአዲስ አበባ ያሉ የመንግስት ሆስፒታሎች የዛሬ አርባና ሃምሳ አመት በፊት የተገነቡ  ናቸው። በአፄ ሚንሊክና በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን ከተገነቡት ሆስፒታሎች ውጪ በደርግ ዘመንና በእነዚህ በወያኔዎች ዘመን በአዲስ አበባ የተገነባ አንድም ሆስፒታል የለም። በንጉሱ ዘመንም ጥቁር አንበሳንና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልን እንዲሁም ሌሎች ሆስፒታሎችንና ጤና ጣቢያዎችን ጨምሮ የተገነቡት በህዝብ መዋጮ በመሆኑ የህዝብ ሆስፒታሎች ተብለው መጠራት ይገባቸዋል። ዛራ የአዲስ አበባ የቆዳ ስፋት ከንጉሱ

ዘመን በአስር እጅ ከደርግ ዘመን በአምስት እጅ የጨመረ ሲሆን ከዚህ ጋር የሚመጣጠን ቀርቶ አንድ የህዝብ ሆስፒታል እንኳን መገንባት አልተቻለም። በአዲስ አበባ በየጊዜው እየጨመረ ካለው የህዝብ ብዛት አንጻር የህዝብ ሆስፒታል አለመገንባቱ ወያኔ ለህዝብ ጤና አጠባበቅ በእጅጉ ደንታ ቢስነቱን ያረጋግጣል የሚሉ በርካት ሀኪሞችና ለህክምና ቅርበት ያላቸው ባለሙያዎች ይናገራሉ። ዛሬም በጥቁር አንበሳና በሌሎች ሆስፒታሎች መኝታ አልጋና መደበኛ ህክምና ለማግኘት በየኮሪደሩ እየማቀቁ ህይወታቸው የሚያልፍ ዜጎች ቁጥር በጣም ብዙ ነው። በመንግስት ሆስፒታሎች ውስጥ ሌላው ችግር ለህየወት አጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ መድህኒቶች የሉም። እንደ ኤክስ ሬይ/ራጂ/ አይነት ምርመራዎችና የላብሯቶሪ ምርመራዎች ብዝዎቹ የመንግስት ሆስፒታሎች በተሟላ መልኩ የላቸውም። በህክምና ላይ ብዙ ልምድ ያላቸው ሀኪሞች ደሞዛቸው አነስተኛ በመሆኑ ወድ ግል ሆስፒታሎች በብዛት ይኮበልላሉ። ወያኔ በህክምናው አስመዘገብኩ የሚለው ለትላልቅ የወያኔ አባሎችና ባለሥልጣኖች መታከሚያ የሚሆኑ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከለኛ ገቢ ያለውን ጨምሮ ሊታከምባቸው የማይቻሉትን የግል ሆስፒታሎች ነው። እነዚህ ሆስፒታሎችም ቢሆኑ እንኳንስ ከአፍሪካ ከጎረቤቶቻችን ከኬንያ ከሱዳን እነዲሁም ከዑጋንዳ ጋር ሊወዳደሩ የማይች በመሆናቸው በየጊዜው አቅሙ ያላቸው በሽተኞች ወደ አረብ አገሮች፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኬንያ፣ እንዲሁም እስያና አውሮፓ ለህክምና የሚጓዙት። ወያኔ ጤና አጠባበቅን ለፖለቲካ ጥቅሙ መጠቀሙ መታወቅ እነዳለበት ጉዳዩ የቀረቀራቸው ዜጎች እየተናገሩ መሆኑን ተረድተናል፡፡በሕክምናው ዘርፍ ያለው ወድቀት በሰፊው ሕዝብ እሮሮ ያሰማበት መሆኑና ሕዝብም የጤናው ዘርፍ የንግድና የገቢ ምንጭ መሆኑ ዋና እየሆኑ መምጣቱ ተጠቁሟል፡፡ በሌላ በኩል ለጤና ሰራተኞች የደሞዝ ጭማሪ ተሰጠ ከተባለ በኋላ ክልሉ ይህን ጭማሪ ሰረዘው መባሉም መታወቅ አለበት፡፡

የወያኔ አገዛዝ ከቻይና መንግስት ጋር በጥቅማ ጥቅም በሰፊው መያያዙ የታወቀ ነው፡፡ የቻይና ኩባንያ በቴሌኮሙዩኒኬሽን መስክ የተሰጠው ኮንትራት ሁሉ ጥሩ ውጤተ ባያመጣም አዲስ የአንድ ቢለዪን ዶላር ማለትም የ10 ቢሊዮን ብር ኮንትራት ወያኔ ለቻይና ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ በ.ዙ ሚለዮን ወደ ወያኔ ባልስልጣኖች ካዝና በጉቦ መልክ ገብቷል፡፡ ከዚህ በተያያዘ ም የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ልጆቻቸውን ወደ ቻይና ለትምህርት እየላኩ መሆናቸው እየታየ ነው፡፡ መለስዘ ስሮዊ ሴት ልጁ በእንግሊዙ ኦክስፎርድ ትገባ ዘንድ እንድርያስ እሸቴ ሽኒ ደብዳ ቤ እንዲፅፍ ቢያደርግም መግባት ስለተሳናት በዚያው ለንዶን ወጣ ብላ ትምህርት ብተቀጥልም የነ አርከበ ፣የነ ሰብሐት ነጋ ፣ የነ ቴድሮስ ሀጎስ ልጆች ግን ቻይና ለትምህረት መላካቸው ደግሞ የሚታወቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሀገራችንን ጫካ እያስጨፈጨፈና የሀገሪቷን የአካባቢ ደህንነት እያጠቃ ያለው ወያኔ መሪ ስለ አካባቢ ደህንነት በሚካሄድ ጉባዔ በዴንማርክ መጋበዙ አግባብ የለውም ሲሉ ብዙዎች ተችተዋል፡፡

በማጠቃለል ደረጃ -- ዛሬ የሀገራችን ዋና ዋና ጥያቄዎች ስንል የመጪው ምርጫ የሚል አይደለ ም፣ ሊሆንም አይችልም። ረሀብ 14 ሚሊዮን ሕዝብን እያጠቃ ነው። ወያኔ በረሀቡ የተነሳ አንድ ዕንቁላል 2 ብር ስለሚሸጥ የገጠሩ ሕዝብ ከበረ ብሎ ሊያላግጥ የሚሞክረው መጋለጥ አለበት። የኑሮ ውድነት ሕዝብን እያሰቃየ ነው። የሀገራችን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ተሰጥቷል። የሀገራችን መሬት ለባዕዳን ተሸጧል። የኢትዮጵያ አብላጫው ሕዝብ በወያኔ እየተሰቃየ ነው። እነዚህና መሰል አበይት ጥያቄዎች አሉ። ብዙ ሺ የፖለቲካ እስረኞች ገና አልተፈቱም። ምርጫ ከተባለም የምርጫው ህግና የምርጫ ኮሚሽን አሁንም በወያኔ ቁጥጥር ናቸውና በስነ ስረፓቱ ስምምነት ቀልድ ነው። በመሆኑም በወያኔ ምርጫ መካፈል አለመካፈል ዋና ጥያቄ አይደለም። ወያኔ ምርጫውን ያሸንፋል፣ ለተለጣፊዎቹም የተወሰነ ወንበር ይለግሳል። የግንቦቱ ውጤት ዛሬ በጥቅምት ይታወቃል። ለከረመ ቁስላችንም መድሀኒቱ ያው የትላንቱ ትግል ብቻ ነው። አቋራጭ ፍለጋው ከቶም አይበጅም።